# ዋሽራ ፬

## የሥራ መመሪያ

Abass Alamnehe
Senamirmir Project
http://www.senamirmir.com

Copyright (c) 2006 abass alamnehe, Senamirmir Project.
Permission is granted to copy, distribute and/or modify this document under the terms of the GNU Free Documentation License, Version 1.2 or any later version published by the Free Software Foundation; with no Invariant Sections, no Front-Cover Texts, and no Back-Cover Texts. A copy of the license is included in the section entitled "GNU Free Documentation License".

# መግቢያ

ዋሸራ ከተለያዩ ፕሮግራሞች ጋር ራሱን አዛምዶ በኢትዮጵያ ፊደል ልዩ ልዩ የኮምፕዩተር ሥራዎችን ለማካሄድ ይረዳል። ዋሸራ 4.0 ሁለት ክፍሎች አሉት፤ እነሱም የኢትዮጵያ ፊደል ፎንቶች (WashRa Fonts) እና የፊደል መምቻ ሥርዓት (keyboard layout) ናቸው። ለጊዜው የዋሸራ የፊደል መምቻ ሥርዓት የሚሠራው <u>ከዊንዶስ 2000 ፣ XP ፣ እና 2003 Server</u> ጋር ብቻ ነው። ፎንቶቹን ግን ያለምንም ችግር ሌሎች የኮምፕዩተር ሲስተሞች ላይ መጠቀም ይቻላል። ወደፊት የፊደል መምቻው ሥርዓት ለሌሎቹም ጭምር ይታሰብበታል። በአጠቃላይ ዋሸራ 4.0 የሚሠራው ዩኒኮድን ከሚቀበሉ ፕሮግራሞች ጋር ብቻ ነው። ይህ ለተጠቃሚውም ሆነ ለሶፍትዌር አዘጋጆች ልማት አለው። መልክቶችን መለዋወጥና ሰነዶችን መቀባበል ከመቸውም ጊዜ በላይ ቀላል ያደርገዋል።

ዋሸራ 4.0 ካለፉት የዋሸራ ወጦች (versions) ጋራ ስምምነት የለውም። ፎንቶቹ ሙሉ በሙሉ <u>በዩኒኮድ</u> ደንብ ብቻ የሚሠሩ ናቸው። ይህ ምን ማለት ነው? በቀድሞ ዋሸራ የተዘጋጁ ሰነዶችንና ሌሎች ሥራዎችን በእነዚህ ፎንቶች መክፈት ወይም መጠቀም በፍጹም አይቻልም። በአንጻሩ በ4.0 የተዘጋጁ ሥራዎችን በቀደሞ የዋሸራ ፕሮግራሞች መገልገል በፍጹም አይቻልም።

ስለዚህ አንባቢውን በጥብቅ የምናሳስበው ከቁጥር 4.0 በታች የተጻፉ ሥራዎች ካሉ፥ በዛው በተጻፉበት ቁጥር መጠበቅ። ነገር ግን አዲስ ጽሑፎችን ወይም ሥራዎች በቁጥር 4.0 ማዘጋጀት። ቍጥር 4.0ን ከ3.2 ወይም ከ3.1 ጋራ አብሮ አንድ ማሽን ውስጥ መቅዳት ይችላል። በፕሮግራሞቹ ሆነ በፎንቶቹ መካከል ግጭት አይፈጠርም።

ዋሸራ 4.0 በጂ/ፒ/ኤል ሕግ መሠረት በነፃ የሚሰራጭ ሥራ ነው። ተጠቃሚዎች በጂ/ፒ/ኤል ሕግ መሠረት በነፃ መገልበጥና ማሰራጨት ይችላሉ፤ ነገር ግን መሸጥ ወይም መለወጥ ግን በፍጹም አይፈቀድም።

# የቅጂው ሂደት

የዋሸራ 4.0 ስርጭት ከሞላ ጐደል የሚካሄደው በኢንተርነት ነው። ስለሆነም ይህ መመሪያ ያንን መሠረት ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜ፥ ተጠቃሚዎች በግል በልዩ ልዩ የዲስክ ዓይነቶች ካሰራጩት የቅጂው ሂደት በትንሹ ይለይ ይሆናል። የቅጂው አካሄድ ደረጃ በደረጃ ይህ ነው።

1. የመጀመሪያው ተግባራችን መሆን ያለበት የዋሸራን ፋይል ከኢንተርነት ሥነ ምርምር አድራሻ መገልበጥ ነው። ይህ አስፈላጊ የሚሆነው ፋይሉ ከሌለን ነው። ገጹ ላይ በተሰጠው መመሪያ መሠረት «washra4-0.exe» ወደ ግል-ኮምፕዩተራችን ደስክታፕ (desktop) ላይ እንገልብጥ። ይህ ፋይል በዚፕ መልክ የተቀረጸና ራሱን በራሱ መፍታት (decompress) የሚችል ነው።

   http://www.senamirmir.com/projects/typography/washra.html

2. የ«washra4-0.exe» ፋይል ከደስክታፑ ላይ በሁለት ጠቅታ እናስነሳ። ከዚህ በታች የተሰጠውን ሥዕል የሚመስል መስኮት ይከፈታል። ከተከፈተው መለስተኛ መስኮት የBrowse በተንን እንጫንና ደስክታፕን (Desktop) እንምረጥ፤ ቀጥሎ የUnzip በተንን እንጫን። የዋሸራ ፋይሎች አሁን ደስክታፑ ላይ ይቀመጣሉ ወይም ይፈታሉ።




3. ወደ ዊንዶስ ደስክታፕ (Desktop) እንሂድና የwashra4-0ን ማኅደር እንከፈት። ተቀጥያቸው «msi» የሆኑ ሁለት ፋይሎች አሉ። ተቀጂ ፋይሎቹ እነዚህ ናቸው። በቅደም ተከተል ሁለቱን ፋይሎች ከዚህ በታች በተሰጠው መመሪያ መሠረት እንቀዳለን።
4. የዋሸራ ፎንቶች መቅዳት፤
   a. የ"Washra4-0-Fonts.msi" በሁለት ጠቅታ እናስናሳ። ቀጂው ፕሮግራም ሥራውን በመጀመር ከዚህ በታች የሚታየውን መስኮት ይከፍታል። በNext ጠቅታ ወደሚቀጥለው ሂደት እናምራ።



b. አሁንም እንደገና በNext ጠቅታ የቅጂውን ሥራ እናራምድና ሂደቱ ሲጠናቀቅ የCloseን በተን በመጫን የዚህን የቅጂ ሥራ እንፈጽም።

5. የዋሽራን የፊደል መምቻ ሥርዓት መቅዳት፤

a. ወደ ደስክታፑ እንመለስና፥ ከwashra4-0 ማኅደር «Washra-Keyboard-Layout.msi»ን በሁለት ጠቅታ እናስነሳ። ቅጂው ያለምንም ችግር ከተጠናቀቀ ያንን የሚገልጽ መስኮት ይከፈታል። የተከፈተውን መስኮት በClose ጠቅታ ከዘጋን በኋላ እንደሚከተለው ወደ ቅኝቱ እናምራ።
b. ከዊንዶስ መስኮት፥ የStartን በተን ጠቅ እናድርግ።
c. ከሚዘረጋው ሜኒዩ Control Panelን እንምረጥ።
d. ከተከፈተው የControl Panel መስኮት፥ የRegional and Language ሀይካንን በሁለት ጠቅታ እንክፈት።
e. ከሚከፈተው መስኮት፣ የLanguageን ገጽ እንምረጥ።
f. ከዛ Detail የሚለውን በተን ጠቅ እናድርግ። መለስተኛ መስኮት ይከፈታል። ለተጨማሪ ርዳታ የሚከተለውን ሥዕል እንመልከት።




g. Addን ስንጫን አዲስ መለስተኛ መስኮት ይከፈታል። የKeyboard Layout/IMF የምርጫ ሳጥንን እንጫን፤ ከዛ ከሚዘረጋው ዝርዝር "WashRa-Keyboard-Layout"ን እንምረጥና የOkን በተን እንጫን።
h. ቀጥሎ Language Bar የሚለውን በተን እንጫንና የሚመጡትን ምርጫዎች ሳጥናቸውን በመጥቀስ እንቀበላቸውና የOkን በተን እንጫን። ይህ የዋሽራን የፊደል መምቻ ሥርዓት እንደተፈለገው ለማስነሳት ወይም ለማቆም የሚያስችል መንገድ (Language Bar) ይፈጥርልናል።

i. በመጨረሻ የCloseን በተን በመጫን የLanguage ገጽ ውስጥ እንመለስና የApply በተን በመጫን የቅኝቱን ሥራ እናጠናቅቃለን።

# የተቀዳን መሰረዝ

ወሸራን ማሽናችን ላይ ከቀዳን በኋላ መሰረዝ ወይም ማውጣት ከፈለግን፥ በControl Panel በኩል የግድ መሆን አለበት። ዝርዝር እነሆ።

1. የዋሸራን ፎንቶች ለመሰረዝ፤
   a. ከዊንዶስ መስኮት፥ የStartን በተን ጠቅ እናድርግ።
   b. ከሚዘረጋው ሜኒዩ Control Panelን እንምረጥ።
   c. የAdd or Remove Programን አይካን ሁለት ጠቅታ።
   d. ከፕሮግራምች የስም ዝርዝር ጋራ አዲስ መስኮት ይከፈታል። የስሞቹ ዝርዝር በፊደል ተራ ቅደም የተጠናቀረ ነው፤ ከዛ ውስጥ «WashRa4-0-Fonts"» እንምረጥና የRemoveን በተን እንጫን። በዚህ መንገድ የስረዛውን ሂደት እንፈጽም። አዛው Control Panel ውስጥ እያለን የሚቀጥለውን ስረዛ እናካሂድ።

2. የዋሸራን የፊደል መምቻ ሥርዓት ለመሰረዝ፤
   a. ሥርዓቱን ከመሰረዛችን በፊት ከዊንዶስ አይምሮ ማውጣት አለብን።

      **Regional and Language -> Language -> Detail -> WashRa Keyboard Layout -> Remove -> Ok**

   b. ወደ Control Panel እንመለስ።
   c. የAdd or Remove Programን አይካን ሁለት ጠቅታ።
   d. ከፕሮግራሞች የስም ዝርዝር ውስጥ «WashRa Keyboard Layout» እንምረጥና የRemoveን በተን እንጫን። በዚህ መንገድ የስረዛውን ሂደት እንፈጽም። በመጨረሻ የControl Panelን መስኮት እንዝጋ።

# የዋሽራ ፎንቶች

ዋሽራ 4.0 ዐሥራ ሁለት ፎንቶች አሉት። እነዚህ ፎንቶች የዩኒኮድን 3.0 ደንብ ያከብራሉ። በተጨማሪ ለተጠቃሚዎች ለልዩ ልዩ ሥራዎች የሚያገለግሉ መልኮችና ቅርጾች ይለግሳሉ። አንባቢው እንደሚታዘበው፥ ከዐሥራ ሁለቱ መካከል ሦስቱ የአይታሊክስ ስታይል አላቸው። ለነሱ መጨመር አብይ ምክንያቱ፥ በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ቋሚ ፊደላቱ ወደ አይታሊክ ስታይል ሲቀየሩ የዝንባሌያቸው ድግሪ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ በገጹ ላይ ይተኛሉ። በመሆኑም የመልክና የመነበብ ችግር አለባቸው። የዋሽራ አይታሊክ ፎንቶች ያንን ችግር ያርማሉ።

| የፎንቶች ስም | ናሙና ንባብ |
|---|---|
| Ethiopia Jiret | መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ |
| Ethiopia Jiret Slant | *መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ* |
| Ethiopic WashRa Bold | **መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ** |
| Ethiopic WashRa Bold Slant | ***መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ*** |
| Ethiopic WashRa SemiBold | **መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ** |
| Ethiopic WashRa SemiBold Slant | ***መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ*** |
| Ethiopic Hiwua | መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ |
| Ethiopic Fantuwua | መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ |
| Ethiopic Yebse | **መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ** |
| Ethiopic Wookianos | መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ |
| Ethiopic Tint | መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ |
| Ethiopic Yigezu Bisrat Gottic Goffer | መልክአ ፊደል፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ |

# የዋሸራን ቂጂ መፈተን

ዋሸራን ከተከያዩ ፕሮግራሞች ጋር አጣምሮ የመጠቀሙ መንገድ አንድ አይነት ነው። ስለዚህ ከማንኛውም ፕሮግራም ጋር መወሰድ ያለባቸው ደረጃዎች ልዩነት የላቸውም። እዚህ ላይ በጥብቅ ልንረሳው የማይገባ፥ ዋሸራን መጠቀም የምንችለው ዩኒኮድን ደንብ ከሚያከብሩ ፕሮግራሞች ጋር ብቻ ነው። ለምሳሌ MS Office፣ Open Office፣ Mozilla Thunderbird፣ የዌብ ገጽ ለመንደፍ Dreamweaver እና የመሳሰሉት መጠቀም እንችላለን። ለምሳሌ ያክል ከMS Word ጋራ ዋሸራን እንዴት እንደምንጠቀም አስከትለን እንመልከት።

1. በመጀመሪያ የዋሸራ ክፍሎች ሙሉ በሙሉ ኮምፕዩተራችን ላይ መቀዳት አለባቸው። አለዛ ይህ ክፍል ውጤት የለውም።
2. የወርድን (Word) ፕሮግራም እናስነሳ።
3. በወርድ ሦር ከዋሸራ ፎንቶች መካከል አንዱን  እንምረጥ፤ ለምሳሌ «Ethiopic Hiwua»።
4. አሁን ከLanguage Bar የዋሸራን የፊደል መምቻ ሦርዓት እንምረጥ ወይም የCtrl+Shiftን እንምታ።
5. በሠንጠረዡ እንደሚታየው ፊደላቱን እንጻፍ።

| ስንመታ | h, | hu | hi | ha | hy | he | ho |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ውጤት | ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |

6. ለማሳሳብ ያህል፥ የግእዝ ቤት ፊደላትን ስንመታ የሚታይ ነገር የለም፤ ነገር ግን አራቢ ፊደላትን ስንመታ የተፈለገው ፊደላ ይመጣል። የምንመታቸው ፊደላት ክትትል የማይታወቅ ወይም የተሳሳተ ከሆነ ውጤቱ ያልፈለግነው ፊደል መታያት ይሆናል። እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠር መደናገር ወይም መጠራጠር አላስፈላጊ ነው። የተሳሳተውን ፊደል ገድፎ እንደገና መጻፍ ማከፊያ ነው።
7. ፈተናው እንደተጠበቀው ውጤት ካላመጣ፥ ምክንያቱ የፊደል መምቻው ሦርዓት አለመነሳት ወይም የፎንት ምርጫው አለመሳካት ሊሆን ይችላል።
8. የዋሸራን የፊደል መምቻ ሦርዓት ለማቆም "Ctrl+Shifte" መጫን በቂ ነው።

# የፊደል መምቻ ሥርዓት

ባሁኑ ጊዜ፥ ከሞላ ጐደል የኮምፕዩተር ፊደል መምቻ ሥርዓት ተመሳሳይ ቁከፎችና አሠራር አላቸው። ባጭሩ የቁልፍ መምቻ ሥርዓቶች አንድ አይነት «ያሠራር-ደንብ» አላቸው ብሎ መናገር ይቻላል። የዋሽራ የፊደል መምቻ ሥርዓት፥ እያንዳንዱን የኢትዮጵያ ፊደል ለመጻፍ ሁለት ቁልፎችን በቅደም-ተከተል መምታት ይጠይቃል። ዝርዝሩ በዚህ ክፍል እንመለከታለን።

## የፊደሉን መምቻ ሥርዓት ማስነሳት ወይም ማቆም

የመምቻውን ሥርዓት በሁለት መንገድ ማስነሳት ወይም ማቆም እንችላለን።

1. አንደኛው መንገድ ፥ የCtrl+Shiftን ብቻ በመጫን ሥርዓቱን ማስነሳት ወይም ማቆም ነው። የመጀመሪያው ጭነት ሥርዓቱን ሲያስነሳ የሚቀጥለው ደግሞ ያቆመዋል እናም ይቀጥላል።
2. ሌላኛው መንገድ፥ የLanguage Barን በመጠቀም ነው። የሚቀጥለው ሥዕል እንደሚያሳየው የተፈለገውን የፊደል መምቻ ሥርዓት በመምረጥ ከአንድ ሥርዓት ወደ ሌላ መመላለስ ይቻላል።




## ያመታቱ ቅንብር

የመደበኛ ኪቦርድ ቁልፎች ቁጥር ከኢትዮጵያ ፊደል እጅግ በጣም ያንሳል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ፊደልና በቁልፎቹ መካከል አንድ-ለአንድ ግኑኝነት መፍጠር አይቻልም። ሁለት ቁልፎችን በማጠናቀር ግን አያሌ ፊደላትን መምታት እንችላለን። የፊደላቱ አመታት ሕግና ዘይቤ ይኸን ይመስላል።

1. ከግእዝ ቤት እስከ ሳብዕ ቤት ያሉት ፊደላት የተነባቢና ያናባቢን ቁልፎች አጠናቅሮ በመምታት ይጻፋሉ። አናባቢ ቁልፎቹ፦ «,» ፥ «u» ፥ «i» ፥ «a» ፥ «y» ፥ «e» እና «o» ናቸው።

| | 1st | 2nd | 3rd | 4th | 5th | 6th | 7th |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **Keys** | h, | hu | hi | ha | hy | he | ho |
| **Results** | **ሀ** | **ሁ** | **ሂ** | **ሃ** | **ሄ** | **ህ** | **ሆ** |

2. አናባቢ ወይም አርቢ ቁልፎች ሁለት ሚና አላቸው። አንደኛው የማራባት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የራሳቸውን ፊደል መወከል ነው። ለምሳሌ፦ U==>ሽ ፤ i==>የ ፤ a==>አ ፤ y==>ኀ ፤ o==>ዐ።

3. አምስቱ የዲቃላ ፊደላት በሚከተለው ዘይቤ እንመታለን።

| | 1st | 2nd | 3rd | 4th | 5th | 6th | 7th |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Keys | g1 | g2 | g3 | g4 | g5 | g6 | g7 |
| Results | **ጐ** | | **ጒ** | **ጓ** | **ጔ** | **ጕ** | |

4. የራብዕ ዲቃላ ፊደላት፥ የግእዝ ቤት ፊደላትን በ«/» አስከትሎ ይመታሉ።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Keys | l/ | m/ | r/ | s/ | u/ | b/ | ... |
| Results | ሏ | ሟ | ሯ | ሷ | ሿ | ቧ | ... |

5. የሥርዓተ-ነጥብ ምልክቶች አመታት፤

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Keys | . | ' | " | ; | : | [ | ] |
| Results | ። | ፣ | ፥ | ፤ | ፦ | « | » |

6. የኢትዮጵያ ቁጥሮች ቀጥሎ በተሰጠው ሠንጠረዥ መሠረት ይመታሉ። የቁልፎቹ ቅንብር አመታት እንደሚከተለው ይሆናል። የ«~» ምልክት መትተን ከዚሮ እስከ ዘጠኝ ያሉትን ቁጥሮች ስናስከትል ተዛማጁ የኢትዮጵያ ቁጥር ይወጣል። ለምሳሌ «~+1» ፲ን፤ «~+3» ፴ን ይሰጣናል።

| Keys | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 0 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ` | ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፻ |
| ~ | ፲ | ፳ | ፴ | ፵ | ፶ | ፷ | ፸ | ፹ | ፺ | ፼ |

የዋሸራ የፊደል መምቻ ሥርዓት ቀጥለው በቀረቡት ሠንጠረዦች ተገልጿል።

| | 1st | 2nd | 3rd | 4th | 5th | 6th | 7th | 8th | wa | wi | wa | wee | we | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ' | u | i | a | y | e | o | / | 1 | 3 | 4 | 5 | 6 | |
| h | ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ | | | | | | | |
| l | ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ | ሏ | | | | | | |
| H | ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ | | | | | | | |
| m | መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ | ሟ | | | | | | |
| S | ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ | ሧ | | | | | | |
| r | ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ | ሯ | | | | | | |
| s | ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ | ሷ | | | | | | |
| u | ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ | ሿ | | | | | | |
| q | ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ | | ቈ | ቊ | ቋ | ቌ | ቍ | |
| Q | ቐ | ቑ | ቒ | ቓ | ቔ | ቕ | ቖ | | ቘ | ቚ | ቛ | ቜ | ቝ | |
| b | በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ | ቧ | | | | | | |
| B | ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ | ቯ | | | | | | |
| t | ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ | ቷ | | | | | | |
| c | ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ | ቿ | | | | | | |
| y | ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ | | ኈ | ኊ | ኋ | ኌ | ኍ | |
| n | ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ | ኗ | | | | | | |
| N | ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ | ኟ | | | | | | |
| a | አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ | ኧ | | | | | | |

| | 1st | 2nd | 3rd | 4th | 5th | 6th | 7th | 8th | wa | wi | wa | wee | we |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | , | u | i | a | y | e | o | / | 1 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| k | ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ | | ኰ | ኲ | ኳ | ኴ | ኵ |
| K | ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ | | ዀ | ዂ | ዃ | ዄ | ዅ |
| w | ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ | | | | | | |
| o | ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ | | | | | | |
| z | ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ | ዟ | | | | | |
| Z | ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ | ዧ | | | | | |
| i | የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ | | | | | | |
| d | ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ | ዷ | | | | | |
| D | ዸ | ዹ | ዺ | ዻ | ዼ | ዽ | ዾ | ዿ | | | | | |
| j | ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ | ጇ | | | | | |
| g | ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ | | ጐ | ጒ | ጓ | ጔ | ጕ |
| G | ጘ | ጙ | ጚ | ጛ | ጜ | ጝ | ጞ | | | | | | |
| x | ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ | ጧ | | | | | |
| C | ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ | ጯ | | | | | |
| P | ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ | | | | | | |
| v | ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ | ጿ | | | | | |
| V | ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ | | | | | | |
| f | ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ | ፏ | | | | | |
| p | ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ | | | | | | |

# የፊደል መምቻ ሥርዓቱ በሥዕል

